https://www.path-2-happiness.com/am

‹‹ከወንድ ወይም ከሴት፣እርሱ አማኝ ኾኖ በጎን የሠራ፣መልካም ኑሮን በእርግጥ እናኖረዋለን፤ይሠሩትም ከነበሩት ነገር በመልካሙ ምንዳቸውን እንመነዳቸዋለን::››[አል ነሕል፡97]

መልካም ሥራ ከእምነት ጋር ውጤቱ በዚህች ምድር ላይ ጥሩ ሕይወት ነው:: ጥሩ ሕይወት ግን የግድ በገንዘብና በሀብት የተደላደለ ሊሆንም ላይሆንም ይችላል:: መልካም ሕይወት ሆኖ ሀብትና ቁሳዊ ጸጋ የሌለበት ሊሆን ይችላል:: በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ ከገንዘብ ውጭ ሕይወትን መልካምና በጎ የሚያደርጉ ብዙ ነገሮች አሉ:: ከነዚህ መካከል ራስን ከአላህ (ሱ.ወ) ጋር ማስተሳሰር፣በርሱ ላይ መተማመን፣በርሱ ጥበቃና ረድኤት መጽናናትና መረጋጋት አንዱ ነው:: ሌላው ጤንነት፣በተሰጠው ጸጋ መርካት፣በረከት፣የሕሊና እርካታ፣ቤተሰባዊ ደስታና ፍቅር፣በሰሩት በጎ ተግባር መደሰትና በሕሊና እና በአነዋነዋር ላይ የሚያሳድረው በጎ ተጽእኖ ሲሆን ገንዘብ ከነዚህ አንዱ አላባ ብቻ ነው:: አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

{ٱلۡمَالُ وَٱلۡبَنُونَ زِينَةُ ٱلۡحَيَوٰةِ ٱلدُّنۡيَاۖ وَٱلۡبَٰقِيَٰتُ ٱلصَّٰلِحَٰتُ خَيۡرٌ عِندَ رَبِّكَ ثَوَابٗا وَخَيۡرٌ أَمَلٗا ٤٦} [الكهف: ٤٦]

‹‹ገንዘብና ወንዶች ልጆች የቅርቢቱ ሕይወት ጌጦች ናቸው፤መልካሞቹም ቀሪዎች (ሥራዎች)፣እጌታህ ዘንድ በምንዳ በላጭ ናቸው፤በተስፋም በላጭ ናቸው::››[አል ከህፍ፡46]

ልብ አላህ (ሱ.ወ) ዘንድ እጅግ ታላቅ፣ብጹእ እና ቋሚ ከሆነ ነገር ጋር ሲተሳሰር፣የሕይወት ጥሩነት ሌላ ትርጉም፣ደስተኝነትም ሌላ ትርጉም ይኖራቸዋል::

የሰው ልጅ እምቢኝ ብሎ ካፈነገጠ ግን፣ቀጣይነት ባለው ሁኔታ የሚዳክርበትን የአለመታደል እና የመረገምን ሁኔታ ለራሱ ወዶ ተቀብሏል ማለት ነው:: በቁጭት ልብን በሚያደማ ሀሳብ፣በጭንቀትና በሀዘን ባህር ሰምጦ ብኩን ለመሆን ቆርጧል ማለት ነው:: አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

{فَمَن يُرِدِ ٱللَّهُ أَن يَهۡدِيَهُۥ يَشۡرَحۡ صَدۡرَهُۥ لِلۡإِسۡلَٰمِۖ وَمَن يُرِدۡ أَن يُضِلَّهُۥ يَجۡعَلۡ صَدۡرَهُۥ ضَيِّقًا حَرَجٗا كَأَنَّمَا يَصَّعَّدُ فِي ٱلسَّمَآءِ}[الأنعام: ١٢٥]

‹‹አላህም ሊመራው የሚሻውን ሰው ደረቱን (ልቡን) ለእስላም ይከፍትለታል፤ሊያጠመውም የሚሻውን ሰው ደረቱን ጠባብ ቸጋራ፣ወደ ሰማይ ለመውጣት እንደሚታገል ያደርገዋል::››[አል አንዓም፡125]

አላህ ሸሪክ የሌለው አንድ አምላክ መሆኑን አረጋግጦ የተቀበለ ሰው፣የሕሊና እረፍት፣ውስጣዊ እፎይታና መረጋጋትን ያገኛል:: አላህ ያጠመመው ሰው ግን - አላህ ይጠብቀንና - ልቡ የጠበበና የጨነቀው፣በሀዘንና በቁጭት የተወረረ፣ውስጣዊ ሰላምና መረጋጋት የራቀው ይሆናል:: ይህም በተውሒድ ያመነና በአላህ አሻርኮ የጠመመ ሰው ምሳሌ ነው:: አላህ (ሱ.ወ) ሌላ ምሳሌ ሲሰጥ እንዲህ ብሏል፦

{ضَرَبَ ٱللَّهُ مَثَلٗا رَّجُلٗا فِيهِ شُرَكَآءُ مُتَشَٰكِسُونَ وَرَجُلٗا سَلَمٗا لِّرَجُلٍ هَلۡ يَسۡتَوِيَانِ مَثَلًاۚ ٱلۡحَمۡدُ لِلَّهِۚ بَلۡ أَكۡثَرُهُمۡ لَا يَعۡلَمُونَ ٢٩}[الزمر: ٢٩]



‹‹አላህ በርሱ ተጨቃጫቂዎች የኾኑ ተጋሪዎች ያሉትን ባሪያና፣ለአንድ ሰው ብቻ ንጹሕ የኾነን ባሪያ (ለሚያጋራና ባንድነቱ ለሚያምን ሰው) ምሳሌ አደረገ፤በምሳሌ ይተካከላሉን?፤ምስጋና ለአላህ ይገባው:: በውነቱ አብዛኞቻቸው አያውቁም::››[አል ዙመር፡29]

የሙሽሪክ ሰው ምሳሌ፣አንዱ ሂድ ሌላው ተቀመጥ ሲለው ሦስተኛው ቁም የሚሉት ዓይነት ክፉ ዐመል የተጠናወታቸው ተጨቃጫቂ ጌቶች ያሉት ሰው ምሳሌ ሲሆን፣በዚህም የአካልም ሆነ የአእምሮ እረፍት አጥቶ እንደተረበሸ ይኖራል:: በአላህ አንድነት የሚያምን ሰው ምሳሌ ደግሞ ለአንድ ጌታ ብቻ ታማኝ ተገዥና ታዛዥ የሆነ ሰው ምሳሌ ነው:: ሁለቱ እኩል ሆናሉን?! አላህ (ሱ.ወ) አንድ ጌታ አንድ አምላክ ነው፤ከርሱ በስተቀር ሌላ እውነተኛ አምላክም ሆነ ሌላ እውነተኛ ጌታ የለም:: ሁሉም ምስጋና እና የላቀ ውዳሴ ለርሱ ይሁን:: እርሱን የማያውቁት ግን በከፍተኛ ውስጣዊ ግጭትና ቀውስ፣በሀሳብና በጭንቀት፣በግራ መጋባት፣በመደናበርና ራስን በማጥፋት አስከፊ ሁኔታ ውስጥ ይኖራሉ::

## ራስን መግደልና ሃይማኖት

‹‹በዓለም ጤና ድርጅት (WHO) ኤክስፐርት የሆኑት ዶክተር ጆስ ማንዌል እና ተመራማሪ አሌሳንድራ ፍሊሽማን ራስን በመግደልና በሃይማኖት መካከል ያለውን ግንኙነት አጥንተው፣ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በተረጋገጠ ሳይንሳዊ ምርምራቸው ቀጥሎ በሰፈረው ሰነድ ውስጥ በተካተተው ውጤቱ ላይ ደርሰዋል፦

A global perspective in the epidemiology of suicide

